# ኢሕአዴግ በሕዝባችን ላይ የሚፈጽመው አሠቃቂ ግድያ፣ እሥራትና እንግልት በአስቸኳይ ይቁም!

*(ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ)*

መድረክ የሀገራችንን ወቅታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ብልሹና አሳሳቢ ሁኔታዎችን አስመልክቶ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ደጋግሞ መግለጫዎች ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል። ሆኖም ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ኢትዮጵያን በብቸኝነት ሲገዛ የቆየው የኢሕአዴግ መንግሥት ማሳሰቢያዎቻችንን አልሰማም በማለትና ለጥያቄዎቻችን መልስ አልሰጥ በማለት፣ አሻፈረኝ ብሎ በትዕቢት በመሞላት በሕዝብና ሀገር ላይ ጥፋት ማድረሱን ቀጥሎበት፣ እነሆ ዛሬ ታላቋን ሀገራችንን ከማትወጣበት አረንቋ ውስጥ እየከተታት ይገኛል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ውስጥ ሲካሄድ የቆየውን ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማስቆም መንግሥት የሚወስዳቸውን የግዲያና የአፈና እርምጃዎች በሚመለከት፣ መድረክ መግለጫዎችን በማስጠትና ለሀገሪቱ ጠ/ሚኒስትር በቀጥታ ደብዳቤ በመፃፍ፣ አማራጭ መፍትሄ ሀሳቦችን ጠቁሟል፤ ሁኔታዎቹ በሕገ-ምንግሥቱ መሠረት በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ እንዲሰጣቸውም ጥያቄዎችን ሲያቀርብ ቆይቶአል፡፡ ያ ሁሉ የመድረክ ጥረት ኢሕአዴግ ሕግንና ሕገ-መንግሥታዊነትን አክብሮ፣ ለሕዝቡ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት፣ በቅርቡ የታየው አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጥሮ፣ በሀገርና በሕዝብ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አርቆ በማስተዋል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አምባገነንነትን መርሁ ያደረገውና የሕዝብን ሕጋዊና ተገቢ ጥያቄዎች በጦር መሣሪያ መጨ ፍለቅን ሙያዬ ብሎ የሚኩራራው ኢሕአዴግ፣ በ ጥፋት መን ገዱ ቀጥሎበታል፡፡ በቅርቡም ክቡር ጠ/ሚኒስትሩ በቴሌቪዥን በሰጡት መግለጫዎች፣ ጥያቄዎቹን አንግቦ ሰላማዊ ሠልፍ መውጣት መብቱ የሆነውን ሕዝብ፣ በኃይል ለመጨፍለቅ “በቂ አቂም” እንዳላቸው በመግለጽ መፎከራቸውን መድረክ በታላቅ ትዝብት ተመልክቶታል፡፡ የፎከሩትም አልቀረ፣ የሰሞኑን ሀገራዊ ትርምስና የዜጎች እልቂት አስከትለው እኛም ሁኔታውን በከፍተኛ ሁዘንና ምሬት ለመታዘብ ተገድደናል፡፡ ስለሆነም በመድረክ እምነት፣ በመላው የኦሮሚያ ክልልና እንዲሁም በአማራ ክልል በጎንደርና በባህርዳር ከ ተማዎች ለደረሰ ው የ ዜጎች እልቂት ኃላፊነቱ ከኢሕአዴግ መንግሥት ውጪ ሊሆን አይችልም፡፡

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአምባገነኑ የኢሕአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያው ሥርዓት እየደረሰበት ያለውን ችግር ለመቅረፍና ዘላቂ መፍትሔዎችንም ለመሻት፣ በሕጋዊነት ተመዝግበው፣ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የሚያካሂደው መድረክና ሌሎችም ሀቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የሕዝቡን ትግል ለመምራት ደጋግመው ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ሰላማው ሰልፎች ቢጠሩም ሥርዓቱ “ዕውቅና አይሰጣችሁም” እያለ መኖሩ የሚታወቅ ነው፡፡ ሕጋዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሕዝቡን ብሶት እንዳያሰሙና ትግሉንም እንዳይመሩ

በተከለከለበት ሁኔታ ነው ሕዝቡ የመሰብሰብና የመሰለፍ ተፈጥሮአዊና ሕገ-መንግሥታዊ መብቱን ተጥቅሞ፣ ዓለም ጉድ ያለውን እንቅስቃሴ፣ ሞት ሳይፈራ በእምቢታ ወደማካሄዱ እርምጃ ውስጠ የገባው፡፡ የሕዝባዊ እምቢታዎች ክስተት በቅርቡ የተከሰተ ብቻ ሳይሆን፣ ላላፉት ሃያ አምስት ዓመታት በኢሕአዴግ እየተካሄዱ የቆዩ በሕዝቦች ላይ የደረሱ የመብት ረገጣዎች ክምችት ውጤቶች ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም በ1992 ዓ/ም ምርጫ ኢሕአዴግ በሀዲያ ዞን በተሸነፈበት ወቅት ያካሄደው ጭፍጨፋና ዜጎችን ለስደት መዳረጉ፣ በጋምቤላ ክልል በአኝዋክ ሕዝብ ላይ የተፈፀመው ጭፍጨፋ፣ በቅርቡም በኮንሶ ሕዝብ ላይ የተፈፀመው አፈና እና ዜጎችን ወደ "ክልልህ ግባ" በማለት ከየመኖሪያ አካባቢያቸው የማፈናቀሉ እርምጃዎች ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሽ የሚሆኑ የኢሕአዴግ ሥርዓተ መንግሥት ወንጀሎች ናቸው፡፡ ለዚህ ሁሉ ያበቃው ኢሕአዴግ በኃይል እንጂ በዴሞክራሲያዊ አግባብ ሕዝቡ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መፍትሔ የመስጠት ባህሉም ሆነ ባሕሪ የሌለው በመሆኑ፣ የሀገራችን ችግሮች እየተከማቹና እየገዘፉ መጥተው ዘሬ ከሚገኙበት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡

ስለሆነም ይህ ሰሞኑን እየተካሄደ ያለው ጅምላ የዜጎቻችን ጭፍጨፋና በገፍ የሚካሄደው ሕገወጥ እሥራትና ማሳደድ በራሱ በኢሕአዴግ መንግሥት ብልሹ አስተዳደርና የፖሊሲ ስሕተትና ክስረት የተከሰተ መሆኑን መድረክ ይገነዘባል፡፡ በአንፃሩም ሕጋዊ የሆነ የመብት ጥያቄ ይዞ ብሶት ፈንቅሎት ለሰልፍ የወጣውን ሕዝብ ለመጨፍለቅ "በቂ ዐቂም አለኝ" የሚለው የኢሕአዴግ መንግሥት፣ አንድ ጦር ያለው አካል ከሌላ ጦር ጋር ተዋግቶ ያሸንፍ እንደሆነ እንጂ ሕዝብን ማሸነፍ እንደማይቻለው ያለተገነዘበ ይመስላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የታጠቀን ኃይል አዝምቶ ዜጎች ላይ ያደረሰው ጉዳት ከነፃው የመገናኛ ብዙሃን ዕይታና ከዓለም ማህበረሰብ ዕውቀት ውጪ ሆኖ ተዳፍኖ እንዲቀር በሚወስደው እርምጃ የሚተማመን እንደመሆኑ፣ ጥረቱ ሁሌ የሚሳካለት ቢመስለውም፣ በአሁኑ ወቅት ሕዝባችን በነፍሱና በደሙ የከፈለው መስዋዕትነት የተባበሩት መንግሥታትን የሰብዓዊ መብት ዋና ኃላፊን ግንዛቤ ማግኘቱና የኢሕአዴግንም መንግሥት የዓለም አቀፍ አጣሪ ቡድን ሁኔታውን እንዲያጣራ ፈቃደኛ መሆን እንዳለበት ጥያቄ እያቀረቡ መሆናቸው ኢሕአዴግን ሊያሳስበው የሚችል አዲስ ክስተት ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ካለፈችባቸው የፖለቲካ ሥርዓት ለውጦች መራር ታሪክ ከመነሳት፣ መድረክ ፖለቲካዊ ለውጥ መምጣት ያለበት በሰላማዊ አግባብ፣ በነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒ ምርጫ፣ በሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ ውሣኔ መሆኑን በፕሮግራሙ ማስቀመጡን ማስታወስ እንወዳለን፡፡ ይኸ እንዳለ ሆኖ እንደ ኢሕአዴግ ያለ አምባገነን ፓርቲ ሕዝብ በነፃ የሚሰጠውን ውሣኔ እንዲቀበል በተለያየ ስልት ሕዝቡና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጫና መፍጠር እንደሚኖርባቸው ደግሞ ግልጽ ነው፡፡ አሁንም እየተቀጣጠለ ያለው የሕዝቡ የእምቢታ እንቅስቀሴ ምክንያቱ ራሱ ኢሕአዴግ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ይኸውም ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ መድረክን ጨምሮ፣ በተደጋጋሚ ባለው ሥርዓት ላይ ተቃውሟቸውን ለመግለጽ ሕዝባዊ ስብሰባዎችንና ሰልፎችን ለማካሄድ ያደረጓቸው

ሕጋዊ ሙከራዎች በኢሕአዴግ በመክሸፉ ምክንያት፣ ሕዝቡ በመቆጣትና የያለፈው የግንቦት 2007 ምርጫ ውጤት በኢሕአዴግ መዘረፍ ያስከተለው ቁጣ መሆኑን ኢሕአዴግ እየመረረውም ቢቀበል ጥሩ ትምህርት ይሆነዋል እንላለን፡፡

በሀገራችን የመንግሥት የሥልጣን ሽግግርን በሚመለከት፣ መድረክ በምርጫ ተወዳድሮ ቢያሸንፍ እንኳን፣ ኢህአዴግ ሁሉንም ሥልጣን ብቻውን ጠቅልሎ ሌሎችን በማግለል ሀገራችንን በፈላጭ ቆራጭነት የሚገዛበት ሁኔታን አደገኛነት በመገንዘብ፣ በምትኩ ከሕዝቡ የተወሰነ ድጋፍ ያገኙትንና በምርጫው ለመሳተፍ የኢህአዴግ ማዕቀቦች ያገለላቸውን የፖለቲካ ኃይሎች ጭምር በመንግስት አስተዳደር ውስጥ የሚያሳትፍ የሽግግር ተልዕኮ ያለዉ መንግሥት በማቋቋም፣ ለሀገራችን መሰረታዊ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ የመስጠት ዕቅድ ማስቀመጡን ማስታወስ እንወዳለን፡፡ ለዚህም ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበት፣ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ የሠፈነባት፣ በብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ላይ ተመስርታ የግለሰብ መብትም የሚከበርባት ኢትዮጵያን ለመገንባት በሰላማዊ አግባብ እንደሚታገል አስቀምጧል፡፡

በሌላው አንፃር የሀገራችን መገለጫ የሆነውን ብዝሃነትንና ይህም የሚጠይቀውን የሁሉንም የሀገሪቱን ሕዝቦች ተሳትፎና ይሁንታ ባገኘ መልክ ለሀገራችን መሠረታዊ ችግሮች መፍትሔ በጋራ የመሻትን አስፈላጊነት ወደ ጎን በመግፋት፣ የተወሰኑ ብሔር/ብሔረሰብ ታጋዮች ብቻ መፍትሔ ማምጣት እንደሚችሉ አድርገው ሕዝቦቻችንንም ዓለምን የሚያሳስቱ ወገኖች፣ ከተባበረ የትግል አጀንዳ አዘናጊ ከሆነውና ሀገር በታኝም ሊሆን የሚችል አስተሳሰባቸውን ከማሰራጨት እንዲቆጠቡ ማሳሰቡ ተገቢ ነው እንላለን፡፡

ዛሬ በሀገራችን እየተካሄደ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንደ ወትሮው በኢሕአዴግ ሊደፈጠጥ እንዳልተቻለ በተግባር እየታየ ነው። ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ ጉዳዩን እያድበሰበሱ በተለያዩ የውጭ አካላት ላይ ማመሃኘትና ዛቻ መሠንዘር ለማንም የማይበጅና ሀገራችንን ወደ ከፋ ሁኔታ የሚከት መሆኑን መንግሥትም ሆነ ሌላውም ወገን በማጤን፣ ኃላፊነት በተመላበት አኳኋን ለመላው ሀገሪቱ ችግሮች አስተማማኝ መፍትሔ መሻቱን ከመቼውም ጊዜ በላይ የወቅቱ ሁኔታ ይጠይቃል።

ስለሆነም፡-

1. ኢሕአዴግና መንግሥቱ የሕዝብ ጭፍጨፋውን፣ በገፍ እሥራቱንና ማሳደዱን በአስቸኳይ እንዲያቆም አጥብቀን እየጠየቅን፣ በሕዝባችን ላይ ጭፍጨፋ ያካሄዱና ለዚህም ትዕዛዝ የሰጡ የመንግሥት ሹማምንት ለፍርድ እንዲቀርቡ፤ጉዳት የደረሰባቸውም ወገኖች ካሳ እንዲከፈላቸው እና በሕዝብ ላይ የደረሰው ጉዳት መጠንም በገለልተኛ የዓለም አቀፍ አካል እንዲጣራ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

2. ሕዝባችን ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች መንግሥት በሕገ መንግሥቱ አግባብ አስቸኳይ ምላሽ በመስጠት ሁኔታዎችን እንዲያረጋጋም አጥብቀን እንጠይቃለን።
3. መላው የሀገራችን ሕዝቦችና ለሀገራችን ፖለቲካ ችግሮች የተለያዩ መፍትሔዎች የሚያቀርቡ ወገኖች ሁሉ ኃላፊነትን በተላበሰ መልክ ዘላቂ ሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ ፍለጋ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ በዚህ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።
4. የሀገሪቱ መንግሥት ሆኖ ያለው ኢሕአዴግ መሪዎችም በሀገራችን ያለውን ሁኔታ በአንደበታቸው ሲገለጹ "ችግሩ የራሳችን ግልጽነት ማጣት ነው፤ የመልካም አስተዳደር ችግርም ነው፣...ወዘተ" ያሉትን በማስታወስ፣ ለተከሰቱት ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ፍለጋ ከመድረክና ሌሎች ሀቀኛ ታቃዋሚዎች ጋር፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ክፍት ማድረግን ጨምሮ፣ ውይይትና ድርድር ያለ ቅድመ ሁኔታ እንዲጀምሩ ጥሪ እናደርጋለን።
5. መላው የሀገራችን ሕዝቦች ትግላችው በብሔርና በክልል ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በሀገራዊ የጋራ ችግሮቻችን ላይ ያተኮረ እንዲሆንና ትግላቸውንም ከሁሉም ሕዝቦች ጋር በሰላማዊ መንገድ አቀናጅተው እንዲያካሂዱ ጥሪ እናደርጋለን።
6. መላው ሰላም ወዳድ የዓለም ሕዝቦች በአጠቃላይና በተለይ ከኢሕአዴግ ጋር ወዳጅ የሆናችሁ ዕርዳታ ለጋሽ መንግሥታት፣ በኢሕአዴግ ላይ ተገቢውን ጫና እንድታደርጉና ሀገራችንን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር በሚናደርገው ትግል ከጎናችን እንድትቆሙ ጥሪአችንን እናስተላልፋለን።

ክብር በግፍ ለተሰዉት ወገኖቻችን!

ድል ለሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ትግላችን!

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ

ነሐሴ 6 ቀን 2008 ዓ/ም

አዲስ አበባ